# ህወሓት ወልቃይትን ሕዝቡን ሳይሆን መሬቱን ብቻ ነው የሚፈልገው!

(ጌታቸው ሽፈራው)

ህወሓት ወልቃይትን መሬቱን ነው የሚፈልገው!

አማራ ነን በማለታቸው ንብረታቸውን የተወረሱ የወልቃይት ተወላጆች

1) አቶ ውብነህ በለጠ_ የእህል ወፍጮ
2) ቀኝ አዝማች ገብሩ ገ/መስቀል _ ትራክተር፣ 200 ኩንታል ማሽላ እና ዳጉሳ
3) አቶ አበራ ዘለቀ_ ትራክተር
4) አቶ ዘውዱ ደምስ _ ትራክተር
5) አቶ አለማየሁ በራ_ ትራክተር
6) አቶ ሙላው አለማየሁ_ ትራክተር
7) አቶ ይርሳው ደምስ _700 ሄክታር የእርሻ መሬት (ለ55 አመት ግብር ከፍሎበታል። የተቀማው በ2005 ዓም ነው)
8 ) ሀጅ ኑር ጣሂር_ 675 ሄክታር መሬት (24 አመት ግብርና ከፍሎበታል)
9) ሳልህ በሻ ኢብራሂም_ 300 ሄክታር መሬት (ለ50 አመት ግብር ከፍሎበታል። በ2006 ዓም ሰብሉን ካረመ በኋላ ከእነ ሰብሉ የተቀማ)
10) አቶ ዘሀረዲን አደም_ 500 ሄክታር ተቀምቶ በዚህ ሰበብ ታምሞ ህይዎቱ አልፏል
11) አቶ ገስጥ ዘነበ 20 ሄክታር መሬት
12) አቶ ልዑል ዘነበ 20 ሄክታር መሬት
13) አቶ ተክሌ አለሙ 20 ሄክታር መሬት
14) አቶ ጌትነት እያሱ 20 ሄክታር መሬት
15) አቶ ታሪኩ ዘነበ 20 ሄክታር መሬት

~ከ11ኛ እስከ 15ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት የወልቃይት ተወላጆች መሬት ተቀምቶ የራሱ የእርሻ መሬት ላለው ኪዳነ ማርያም ለተባለ ከአክሱም ለመጣ የትግራይ ተወላጅ ተሰጥቷል።
~በአጠቃላይ የወልቃይት ተወላጆች የቆላ እና የደጋ አነስተኛ መሬታቸውን ጨምሮ እየተቀሙ ቤተሰባቸው ተበትኗል፣ ለስደት ተዳርገዋል። ሀገር ውስጥ የሚገኙትም በስጋት ይኖራሉ። ወልቃይት ውስጥ ገበሬዎች ከመኖርያ ቀያቸው ርቀው የሚያርሱትን የቆላ መሬት እየተቀሙ ለትግራይ ተወላጆች ይሰጣል።
(መረጃው የወልቃይት አማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ ሰነድ ላይ የተገኘ ነው)

---

አማራ ነን በማለታቸው ታፍነው፣ ለ27 አመት የት እንደገቡ የማይታወቁ የወልቃይት ተወላጆች!
ትህነግ/ህወሓት ወልቃይትን መሬቱን ብቻ ነው የሚፈልገው የምንለው ለዚህ ነው። የማንነት ጥያቄ ያነሳ ይታሰራል፣ ይገደላል፣ ታፍነው የት እንደደረሱ የማይታወቁት በርካቶች ናቸው።
ለአብነት ያህልም
ከ1983 በኋላ ታፍነው ደበደዛቸው ካልተገኘው የወልቃይት አማሮች መካከል የተወሰኑት!
1) አቶ ማሙ ዘውዴ
2) አቶ አለባቸው ሙበራቱ
3)አቶ ኃይሉ ልይልህ

4)አቶ አብርሃ ነጋ
5) አቶ አለባቸው ደፍርሻ
6)አቶ ፋንቱ ተገኘ
7) አቶ ማለ ዘነበ
8 ) አቶ ቻሉ ወርቁ
9) አቶ ሰፊ ሲሳይ
10) አቶ በየነ አየልኝ
11) አቶ ማለደ ነጋ
12)ጎሹ ኃይሌ
13) አቶ አለበል ኃይሌ
14) አቶ ሀብቴ ዘነበ
15) ተክሌ ልጃለም
16) ፈጠነ ገብርዬ
17)አዲሱ ጠጄ
18)ሲሳይ ተስፋሁን
19) ዳኘ? ታደለ
20) ማሙ ደስታ
21) መሸሻ ደስታ
22) ሰረበ በተነ ቢተውልኝ
23) የሺበር
24) ወልዴ ያዕቆብ
25) በርሄ ሀጎስ
26) ለምለሙ ፈረደ
27) አቶ የሸተህ አያልነህ
28) ጎይቶም ሀድጉ
29) ገብረስላሴ ረዳ
30) ሀብቴ ይርጋ
31) አቶ ድራር ገሰሰ
32) አቶ ሊላይ ሀድጉ
33) አቶ ርስቃይ ሐይሌ
34) አቶ አሳመነ አታላይ
35) አቶ ተበጀ በቀለ
36) አቶ ሐየሎም ይርጋ
37) አቶ ገሬ ረዳ
38) አቶ አያሌው ሰሙ
39) አቶ ገ/ማርያም ዘለቀ
40) አቶ ፈረደ ዘርዓይ
41) አቶ ገ/መድህን ዘርፉ
42) አቶ ተገኘ ነጋ

43) ቄስ በለጠ
44) አቶ መርዕድ ገ/ሚካኤል
45) አቶ አዳነ ርስቱ
46) አቶ ገብሬ ትርፍነህ
47) ቀኛዝማች ወልዴ ዋስይሁን
48) ሲሳይ ተስፋሁን
49) አረፋይኔ መኮንን
50) ደስታ ልጃለም
51) ፋንቱ ሲሳይ
52) እያሱ አለነ
53) ይበይን ተገኘ
54) አቶ ተካልኝ ተስፋዬ
55) አቶ ሀጎስ አታላይ
56) አቶ አለኸኝ ፀጋዬ
57) ፋንታሁን ገበየሁ
58) እንኳየን ለገሰ
59) አለሙ ለገሰ
60) ርጥበይ አፅብሃ
62) ሙላው ካሳሁን
63)አያሁነይ ወንዳቸው
64) ደረጀ አንጋው
65) አለኸኝ ፀጋየሱስ
66) ወንድም ሀይሌ
67)ሲሳይ
68) አጥማፋ አለማየሁ
69)እንየው አውሃራ
70) አስማማው በለጠ
71) አወቀ ትኩ
72) አደበ
73) አታላይ አለም
74) አስማረ
75) ጠጋዬ
76) ልጃለም ታዬ
77) ገ/መድህን ዘርፉ
78) ተድላ ሀይሌ
79) የመንበሩ ፈረደ ልጅ
80) ምህረት አበበ
81) ንጋቱ ትርፌ
82) አበበ ተፈራ

83)አቶ ገብርሔት ባህታ
84)ዳምጤ ታከለ
85) ተገኘ በላይ
86) አቶ እንዳሻው ታፈረ
87) በየው ቢያድግልኝ
88)አታላይ ዘነበ
89) ገ/መድህን የኋላ
90)ነጋ ተበጀ
91) ይርሳው ዘውዴ
92)ጌታው ታምሬ
93) ተፈራ ሲሳይ
94) ግፋቸው ዳኘው
95) ጌጡ ወሴ?
96)ማማይ ተበጀ
97) ወርቁ አይጠገብ
98) ተካ ተስፋዬ
99) ፈረደ ፀሀይ
100) አለማው ዘነበ
101) ተካልኝ ፀጋዬ
102) ነጋ አስረስ
103) ዋኘው አባጣለው
104) አለቃ ባየ
105) ልዑል መስፍን
ከላይ ስማቸው የተጠቃው "አማራ ነን" በማለታቸው ታፍነው የት እንደደረሱ ያልታወቁ ናቸው። አብዛኞዎቹ ገበሬዎች ናቸው።

---

ማርቆስ አብርሃም እና ግርማቸው ያለው አሁንም አልተፈቱም!
~"የጎቤ መልኬን ስም ተነቅሰሃል፣ የኢትዮጵያን ካርታ ተነቅሰሃል"
~"ኮከብ የሌለው ሰንደቅ አላማ ይዘሃል"
ማርቆስ:_ ኮከብ የሌለው ሰንደቅ አላማ ይዘሃል፣ ጥር 12 የወልዲያን አመፅ መርተሃል ተብሏል። (ማርቆስ ጥር 12 ጎንደር ነበር።) እንዲሁም የሎዛ ማርያም ጥምቀት ርችት ተኩሰሃል ተብሏል።
ግርማቸው:_ የጥምቀት ቀን ኮከብ የሌለው ሰንደቅ አላማ ይዘሃል፣ እጅህ ላይ የጎቤን ስም ተነቅሰሃል፣ ከጀርባው ላይ "ይች ናት ሀገሬ" የሚል የኢትዮጵያን ሙሉ ካርታ ተነቅሰሃል ተብሏል።

---

የወልቃይት ሕዝብ የወጣቶችን ዋስትና ክፍሏል
የወልቃይት ኮሚቴ ሲባል በሰው አእምሮ የሚመጣው የእነ ኮ/ል ደመቀ፣ የእነ አታላይ ዛፌ፣ የእነ መብራቱ ጌታሁን፣ የእነ ነጋ ባንተይሁን፣ የእነ ጌታቸው አደመ፣ የእነ አለነ ሻማ፣ የእነ ተሻገር ወ/ሚካኤል ስም ሊሆን ይችላል።

ነገር ግን የማንነት ጥያቄ እያቀረቡ ያሉ በርካታ ወጣቶችም ተፈጥረዋል፣ ሕዝቡም ጠያቂ ነው! በቅርቡ 9 ወጣቶች የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ክስ ተመስርቶባቸዋል። በቅርቡ ዋስትናም ተጠይቆባቸዋል። ዋስትናቸውን ደግሞ ዶ/ር አብይ ያለው ዳያስፖራ ሳይሆን የወልቃይት ሕዝብ ከ100 ብር ጀምሮ በማዋጣት 140 ሺህ ብር ከፍሎላቸዋል።

ይህን ያደረገው የቃፍታ፣ የሴቲት፣ የአዲረመጥ፣ ጠገዴ ማይጋባ እና ማይካድራ ሕዝብ ሲሆን የዋስትና ገንዘቡን በአንድ ቀን አዋጥቶ ከፍሏል።

የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው እንደ አዲስ ክስ የተመሰረተባቸው ወጣቶች:_

1ኛ ተከሳሽ ፈረደ ሽቱ ኣበጋዝ አድራሻ ዓድ-ረመፅ

2ኛ አባይ ማማይ እጅጉ፣ ኣድራሻ ዓድ-ረመጥ

3ኛ ደሞዘየ መልኬ ሰጣርገው ፣ ኣድራሻ ዓድረመጥ

4ኛ ክብርኣብ ስማቸው የሺወንድም፣ አድራሻ ዓድረመጥ

5ኛ ፈረደ በሪሁን፣ ኣድራሻ ዓድ-ረመጥ

6ኛ ታምራት ደሳለኝ፣ ኣድራሻ ዓድ-ረመጥ

7ኛ እንዳለው ብርሃኔ፣ ኣድራሻ ዓድ-ረመጥ

8ኛ ሞላ አበለይ፣ ኣድራሻ ዓድ-ረመጥ

9ኛ ልኡል ሓጎስ፣ ኣድራሻ ዓድ-ረመጥ

---

ጎንደርን በጨረፍታ አስጎበኝዎታለሁ! አማራ ክልልን ያዩበታል!

(ጌታቸው ሺፈራው)

ጎንደርን ያውቋታል ሲባል ሰምቻለሁ። እኔ ለአንድ ወር ያህል ጎንደር ቆይቻለሁ። እርስዎ ጎንደርን የሚያውቋት የየመከላከያ አመራር ወይንም ባለስልጣን ሆነው ነው። የሚያውቁት የመከላከያ እና የባለስልጣናቱን ጎንደር ነው። የህዝቡን ጎንደር አያውቋትም። በእርግጥም የድሮዋ ጎንደር ከዛሬዋ ትለያለች። ዛሬ መንገድ ላይ እያለፉም ቢሆን ሀቁን በግልፅ ይረዱታል። መረዳት የሚፈልጉና የሚችሉ ከሆነ! ጎንደርን ሲጎበኙ ሆን ተብሎ የደቀቀውን አማራ ክልልን በአንድ ከተማ ላይ ይመለከቱታል! በተለይ የሚከተሉትን ከልብ ከጎበኙ:_

1) መንገዶቹ

ምን ያህል በዘመናዊ መኪና ቢሄዱባቸው፣ ይህን ከአየር መንገድ እንደወጡ የሚረዱት ይሆናል። በአዘዞ በኩል ቢያሳልፉዎት እንዴት ደስ ባለኝ። መንገዶቹ ፈራርሰው አስፓልት የሚባል ነገር የሌለው መሆኑን ሲረዱ "የመጣሁት ሌላ ቦታ ነው?" ማለትዎ አይቀርም። ድሮ የሚያውቁት አስፓልት እንኳን የለም! ከተማ ውስጥ ሳይሆን ቋጥኝ የሚወጡ ይመስልወታል። በታችኛው መንገድ ሲመጡም የሚያገኙት ተመሳሳይ ነው። የሆስፒታሉን መንገድ ባስጎበኝዎት የማያምኑትን ይመለከታሉ!

2) የፋሲሊደስ ቤተ መንግስት

ጎንደር አለኝ ከምትላቸው ቅርሶች መካከል አንዱና ዋነኛው የፋሲለደስ ቤተ መንግስት ነው። በአሁኑ ወቅት የፋሲለደስ ቤተ መንግስት ሰው ደስ ብሎት የሚጎበኘው ሳይሆን "እየፈረሰ ነው" ብሎ ከንፈር የሚመጥለት ቅርስ ሆኗል። በአመት በርካታ ሺህ ዶላሮችን እያስገኘ የወፍ ላባ እና ኩስ እንኳ የሚጠርግለት አልተገኘም። ውጭ ላይ የነበሩት አግዳሚ ወንበሮች ተሰባብረዋል። ግንቡ እየፈረሰ ነው፣ ወለሎቹ ፈራርሰዋል። ቅርሱ ውስጥ የሚፈፀሙትን መቆጣጠሪያ ድብቅ ካሜራ ስለሌለው ግድግዳዎቹ የገባው ሁሉ የተሰማውን የሚፅፍባቸው ሰሌዳዎች ሆነዋል። ከቅርሱ የሚገኘው ገቢ የሚውለው ለፌደራል መንግስቱ መሆኑንም እንዲያስታውሱልኝ!

3/ ጎንደር ሆስፒታል
የጎንደር ሆስፒታል በኢትዮጵያ ቀዳሚ ከሚባሉት ተቋማት መካከል መሆኑን አይረሱትም። ከላይ እንደገለፅኩልዎት በአዘዞ በኩል ወደ ሆስፒታሉ ቢያቀኑ አይንዎትን ማመን ያቅትዎታል። እርስዎ ስለ እናትዎ ያለዎትን ፍቅር በፓርላማው ገልፀዋል። የጎንደር እናቶች ለመውለድ ወደ ሆስፒታል ሲመጡ መንገዱ ከመፈራረሱ የተነሳ ፅንሱ ተዛብቶ የሞቱ እንደአጋጣሚ ሆኖም መንገድ ላይ የወለዱ እንዳሉ ይነግሩዎታል። ወደ ሆስፒታሉ ገባ ቢሉ እናቶች፣ ህፃናት ውጭ ላይ ተኝተው ያገኟቸዋል። ምን አልባት አጠር ሲል በአንድና ሁለት ወር ውስጥ የሚደርሳቸውን አልጋ እየተጠባበቁ ነው።
ይህ ሆስፒታል በትንሹ እስከ 10 ሚሊዮን ሕዝብ ለሚኖርበት አካባቢ ቅርበት ያለው ነው። ነገር ግን በመቶ የሚቆጠሩትን እንኳ በሚገባ እያገለገለ አይደለም። እስርን ካልፈሩ የዚህ ምክንያት ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ባላቸው ግንኙነት ለሆስፒታሉ እርዳታ፣ ልምድና ባለሙያ በማምጣት ይሰሩ የነበሩ ባለሙያዎች ተማርረው እንዲሰደዱ መደረጋቸው የቀሩት ሰዎች ይነግሩዎታል። በተጨማሪም ጠንካራ ሰዎችን ከሆስፒታሉ በማራቅ ለመንግስትዎ የሚመቸውን አቅመ ቢስ ሰራተኛ እንደቀጠሩበት ያጫውቱዎታል። ለአብነት ያህልም ከስር የተዘረዘሩት ባለሙያዎች በሰበብ ከዩኑቨርሲቲ ሆስፒታሉ እንዲርቁ ተደርገው አቅመ ቢስ ካድሬ እንደተተካበት ያጫውቱዎታል። ለምሳሌ ያህልም:_
1ኛ ዶ/ር መሰረት_ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የህፃናት ስፔሻሊስት የነበሩ_ ወደጤና ጥበቃ ሚኒስትር
2ኛ ዶ/ር አበባው_ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ውስጥ ይሰራ የነበረ ወደ ክልሉ ጤና ጥበቃ
3ኛ ዶ/ር ዘኪ_ የጎንደር ሆስፒታል የቀዶ ጥገና ሀኪምና መምህር በአሁኑ ሰዓት ወደ አዲስ አበባ ጥቁር አንበዳ የተወሰደ
4ኛ ዶ/ር ካሳሁን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስታፒል የቆዳ ጥገና ሀኪምና መምህር በአሁኑ ሰዓት ወደ አሜሪካ ሀገር የተሰደደ
5ኛ ዶ/ር ተስፋዬ _ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል_ ትምህርት ሚኒስትር የተዛወረ
6ኛ ዶ/ር አለም ሰገድ _የጎንደር ዩኒቨርሲቲ መምህር ወደ ጤና ጥበቃ
7ኛ ፐ/ር አፈወርቅ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የምርምርና የማህበረሰብ አገልህሎት ምክትል ፕሬዝደንት የነበሩ ወደሳይንስና ቴክኖሎጅ ተዛውረዋል
8ኛ ዶ/ር ኤባ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የማይክሮ ባዮሎጅ ትምህርት ቤት ክፍል ተመራማሪና መምህር_ በአሁኑ ወቅት ወደ ፓስተር ኢንስትቲትዩት
9ኛ ዶ/ር ደሳለኝ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የህብረተሰብና ጤና ትምህርት ክፍል መምህርና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር የነበረ፣ አሁን ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር የተዛወረ
10ኛ ዶ/ር ማህሌት _ የጎንደር ሆስፒታል ስፔሻሊስት፣ ወደ ጳውሎስ የተዛወረች
11ኛ ዶ/ር በየነ _ የጎንደር ሆስፒታል የማክሮ ባዮሎጅ መምህርና ተመራማሪ የነበረ ወደ ፓስተር የተዛወረ
12ኛ ዶ/ር ኤርሚያስ ዲሮ _የጎንደር ሆስፒታል የውስጥ ደዌ ትምህርት ክፍል መምህርና የአባላዘር በሽታ ተመራማሪ ~ወደ አሜሪካ የተሰደደ
ከላይ ለምሳሌ የተዘረዘሩት ባለፈው አምስት አመት ብቻ ወደተለያየ ቦታ ተዛውረው፣ ተማርረው ተሰድደው ሆስፒታሉ ባዶ ሆኗል። አንድ አቅመ ቢስ ካድሬን ወደ ጎንደር ለማምጣት “አትውሰዱን” እየተባሉ የረባ ስራ ወደማይሰሩበት ተቋማት ተዛውተው ሆስፒታሉ ባዶ እንደቀረ ያጫውቱዎታል!
3/ ጎንደርን በነፃ የሚጠቀሙባት ተቋማትን ይጎብኙ

መቼም የፓርቲዎ አጋር ከሆነው ዳሽን ቢራ ፋብሪካ ውጭ ጎንደር ውስጥ ሌላ ፋብሪካ እንደሌለ ይገነዘባሉ። አልፎ አልፎ በከተማው የሚያዩወቸው ግንባታዎች የወልቃይት ተወላጆች ንብረት ናቸው። መቀሌ ሄደው ቢገነቡ ብዙ ነገር እንደሚመቻችላቸው እየተነገራቸው “አንፈልግም” ብለው በጫና የሰሯቸው ናቸው። አልፎ አልፎ ከሚታዩት ውጭ ቀሪዎቹ የቆዩ የህዝብ ህንፃዎች ናቸው። ህንፃዎቹ በወር ከ30 እስከ 100 ሺህ ብር መከራየት የሚችሉ ናቸው። ይሁንና የተለያዩ የመንግስትና የፓርቲ ድርጅቶች እነዚህን ህንፃዎች በነፃ ወይንም ነፃ በሚባል ዋጋ እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። ጥቂቶቹን ልጥቀስልዎት:_

1)ቴሌ
2)መብራት ኃይል
3) ከፍተኛ ፍርድ ቤት
4)ዞን ፖሊስ
5) የከተማው ፖሊስ
6) ዞን አስተዳደር
7)ከንቲባ ፅ/ቤት
8 / ጤና ቢሮ
9)ትምህርት ቢሮ
10) ጉምሩክ
11)ኢንቨስትፕንት ቢሮ
12) የከተማው ፖሊስ ቢሮ
13)የከተማው ፋይናንስ
14) የከተማው ፋይናንስ
15)ባህልና ቱሪዝም ቢሮ
16) ቀበሌ 3 ፅ/ቤት
17) ቻምበር ፅ/ቤት
18)ብሔራዊ ሎተሪ
19)ፖስታ ቤት
20)ጅንአድ
21)አምበሳ ጫማ
22) ጅምላሸቀጣሸቀጥ
23) የሰነዶች ማረጋገጫ
24) የከተማው ሲኒማ ቤት
25) አልማ
26) የወረዳ ፍርድ ቤት
27) ንግድ ባንክ
28) ሜጋ

እነዚህ ተቋማት በወር ከ30 እስከ 100 ሺህ ብር ኪራይ መክፈል ነበረባቸው። በአጠቃላይ ሲታይ የጎንደር ሕንፃዎች ለእነዚህ የመንግስት፣ የህወሓት የንግድ ድርጅቶች፣ የፓርቲ ድርጅቶች በርካታ ሚሊዮን ብሮ ዋጋን በነፃ ሲሰጡ ቆይተዋል። እነዚህ ተቋማት ህንፃ ቢገነቡ ይኖር የነበረው ኢንቨስትመንት እንዲሁ ቀርቷል። በነፃ የሚያገለግሉትን የጎንደር ተቋማት ሲጎበኙ ፋና ሬድዮ ጣቢያ

የሚጠቅምባቸውን የደሴው የንጉስ ሚካኤል ቤተ መንግስት፣ የደብረማርቆሱ የንጉስ ተክለሀይማኖት ቤተመንግስትና ሌሎች ቅርሶችም የንግድ ቤት እንደሆኑ አስታውስዎታለሁ!

4/ ውሃና መብራት

መንግስትዎት ያለ ባለሙያ ስንት ፕሮጀክቶችን ሰርቻለሁ ብሎ ከለፈለፈ በኋላ ፕሮጀክቶቹ መና ሆነው እንደሚቀሩ የጎንደር ውሃ ፕሮጀክት ቋሚ ምስክር ይሆንዎታል። እናቶች፣ ልጆች በጀርባቸው ጀሪካን ተሸክመው ወደ ቀሃ ወንዝ ሲጓዙ አስጎበኝዎታለሁ። የመብራቱን ጉዳይ አንድ ቀን ብቻ በከተማዋ ቢያድሩ በደንብ የሚረዱት ይሆናል!

5/ ነጋዴዎች

አዲስ አበባ ላይ ነጋዴዎችን አነጋግረዋል። በየሱቁ ዞረው ማነጋገር አይችሉም እንጅ ዞረው ቢያነጋግሩ እውነታውን ያዩት ነበር። አንድ ሁለት ነጋዴዎችን ቢጠይቁ ምሬቱን ይነግሩዎታል። ነጋዴዎች ለፌደራል ወይ ለክልሉ መንግስት ግብር የሚከፍሉበት መንገድ አለ። ለፌደራል መንግስቱ የሚከፍሉት "plc" ብለው ሲከፍቱ ነው። ከዚህ በታች ያሉት የሚከፍሉት ለክልሉ መንግስት ነው። ሆኖም ግን የክልሉን ገቢ ፌደራል መንግስቱ (ህወሓት ማለቴ ነው) ሆን ብሎ ቀምቶታል። ለክልሉ የሚከፍሉት በጣም ከፍተኛ ግብር እንዲከፍሉ ተፈርዶባቸዋል። plc ብሎ ያቋቋመ ለፌደራል መንግስት ስለሚከፍል ለክልሉ ከሚለፍሉት ጋር ሲነፃፀር በጣም ቅናሽ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል። በዚህም ምክንያት የአማራ ክልል ገቢ እንዳይኖረው መደረጉን መፍትሄ ለማልሰጣቸው እኔ የነገሩኝን ለእርስዎማ በደንብ ይነግሩዎታል!

6/ የኮ/ል ደመቀ ዘውዱ መኖርያ ቤት የነበረውን

ቀበሌ 18 የሚገኘውን ኮ/ል ደመቀ እስከ ሀምሌ 5 /2008 ዓም ይኖርበት የነበረውን ቤት ከፋሲለደስ ቤተ መንግስትም ቀድመው ቢጎበኙት ብየ እመክርዎታለሁ። 1ኛ እርስዎም የነበሩበት፣ አሁንም የሚመሩት መንግስት በሕዝብ ላይ የፈፀመው ጥቃት ነው። 2ኛ አንድ መከላከል የሚችል ንፁህ ዜጋ ላይ የመንግስት ነኝ የሚል ጦር ይህን የመሰለ ጥቃት ከፈፀመ፣ ለመከላከል አቅም የሌለውን ምን ሊያደርገው እንደሚችል መገመት ይችላሉ። ይህ ቤት መንግስት በአማራው ላይ ለፈፀመው፣ አማራውም በመንግስት መገፋቱ በቃኝ ያለበት ትልቅ ምልክት ነው! መንግስት ለሚፈፅመው አረመኔያዊ እርምጃ ምሳሌ ከመሆኑ ባሻገር ልብ ላለው ለወደፊት ቆም ብሎ ለማሰብ የሚያስችል ምልክት ነው! ከላይ የተጠቀሱት የጎንደር ብቻ አይደሉም። ጎንደርን ለአማራ ክልል መነፀር አድርገው ይጠቀሙበት ዘንድ ነው። ይህ ስል እርስዎ ኢህአዴግ መሆንዎትን ረስቼ አይደለም! ኢህአዴግም ልቦና ይሰጠዋል ብየ አይደለም! ይህ ሁሉ መበደል፣ መበዝበዝ፣ መደህዬት ምን ሊያመጣ እንደሚችል ይገምታሉ ብየ ነው! የወልቃይት ጉዳይ ሌላ ነው! እኔ ከምነግርዎት ይልቅ ስታዲዬም ላይ ይዘመርልዎታል!